የባለ አእምሮ ሥራ እንሥራ

ይኽን ጽሑፍ ለመጻፍ ያነሳሣኝ ነገር በቅርቡ ቤተ ክርስቲያናችንና አባቶቻችን ብዑዓን ሊቃነ ጳጳሳትን አስመልክቶ በተለያዩ የጡመራ ዐውዶች የሚለቀቁ ጽሑፎች ናቸው። እነዚህን ጽሁፎች ትክክል ናቸው ወይም ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸውን አባቶች አስመልክቶ እየተባለ ያለው ነገር ትክክል ነው ወይም ሐሰት ነው ለማለት አይደለም።

በመሠረቱ ሰው የመሰለውንና ያመነበትን ሐሳብ የማቅረብ መብት አለው። ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቸረው የነጻ ምርጫ ፈቃድ አለውና ነው። ይኽን መብቱን ተጠቅም ይኽን ወይም ያንን ደግፎ ወይም ነቅፎ መናገር ይችላል። በሚናገርበት ወይም በሚጽፍበት ወቅት ግን ያ ሐሳቡ በእውነተኛ መረጃ ላይ ስለ መመስረቱ እርግጠኛ መሆን አለበት። እርግጠኛ ካልሆነ ግን ራሱን አሳስቶ ሰሚውንም ሆነ አንባቢውን ሊያሳስት በዚህም ለባልንጀራው መሰናክል ስለ ፈጠረ በእግዚአብሔር ዘንድ ይጠየቃል።

ጌታችን በመዋዕለ ስብከቱ ሰዎች ስለሚናገሩት ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን የሚጠየቁ መሆናቸውን አስተምሯል። ከንቱ ነገርም ለሰሚውም ሆነ ለተናጋሪው አንዳች ምድራዊም ሆነ ሰማያዊ ሕይወት ጠቀሜታ አልባና እውነተኛነት የሌለው ነገር ነው። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ “አትግደል” በሚለው ትእዛዘ እግዚአብሔር ላይ በሰጡት ማብራርያ አንዳንድ ሰዎች ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ሐሳብን በነጻነት ሆነው በጽሑፍ የመግለጥ መብት ተጠቅመው የብዙዎችን ስም በማጉደፍና ነገመና በመግለጥ ቅስምም በመስበር መግደላቸውን ገልጠዋል።

ባለፈው ሳምንት በአንዱ የጡመራ መድረክ የወቅቱን የቤተ ክርስቲያናችንን ሁኔታ ማለት የሽምግልናውንና ስድስተኛውን ፓትርያርክ ለመምረጥ እየተደረገ ያለውን አንዳንድ እንቅስቃሴ አስመልክቶ ተቃውሞአቸውን የሚገልጡትን ወይም የገለጡትን ተቃውሞ መልሰው የሚቃወሙትን በቃለ እግዚአብሔር አስታኮ በማሸማቀቅ ሕዝቡ አንዳች እንቅስቃሴ ከማድረግ ይልቅ በጸሎት ብቻ ችግሩ ይፈታል ብሎ እጁንና እግሩን አጥፎ እንዲቀመጥ የሚያደርጉ ለዚህም የተደራጁ አካላት መኖራቸውን ሳነብ እጅጉን ገርሞኝ ነበር።

www.danielkibret.com

ይኽን ጽሑፍ የጻፈው አካል የመጻፍ መብቱ የተጠበቀ ነው። ግን ፀሐፊው እንደገለጠው ይኽን ለማድረግ የተደራጀ አካል ለመኖሩ ምን ያኽል ርግጠኛ ነው? በትክክል እንደ ተባለውም ያ ተደራጀ የተባለው አካል ካለ ቃለ እግዚአብሔርን የራስን አመለካከት ማሳኪያ አድርጎ በመውሰዱ ከፍርድ ሊድን ይችላልን? ይኽን የተሳሳተ መንገድ እንደ በጎ አካሄድ አድርገው የሚጠቀሙ አንዳንድ ግለሰቦች ቢኖሩ እንኳን ያን ያክል ቦታ ሰጥቶ እንደ አንድ የተደራጀ ቡድን ወይም አካል አግዝፎ በጡመራ መድረክ ላይ መግለጡ ራሱ ለእኔ እንዲህ ዓይነቱን አካሄድ ላላሰቡት ሳይቀር ማሳሰብ መስሎ ይታየኛል።

አሁን አንድ ነገር ብናስብ ጥሩ ይመስለኛል። ቤተ ክርስቲያናችንን አባቶቻችንን የሚያምሰው ችግር አንዳንዶች እንደሚያስቡት አባቶች መንፈሳዊነትን አጥተው ወይም የመንግሥት ጣልቃ ገብነት አይሎ አይመስለኝም። እግዚአብሔርን ያላስደሰትንበት አንዳች ጉድለት ይኖራል ብየ አምናለሁ። እግዚአብሔር ለሕጉና ለፈቃዱ ቀናተኛ አምላክ ነው። በገዛ ደሙ የዋጃቸው ምእመናን ከአሕዛባዊ የኖሮ ሥርዓት ርቀው በቀናነትና በንጽሕና እንዲያመልኩት ይፈልጋል። ይኽ አልሆን ሲል ግን ወደ በጎ ፈቃዱ እስኪመለሱ ድረስ ለማይመች አካሄድ ፈቃዱን ይሰጣል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለክብሯ የማይገባ ነገር ሲፈጸም እኛ ካህናት በንጽሕና ማገልገል ሲሳነን፣ ሥርዓቱ ሲጓደል፣ እምነት ጠፍቶ ማስመሰል፣ መሞዳሞድና መመሰጋገን ሲበዛ እግዚአብሔር ቋንቋችንን ይደበላልቀዋል። ስለ አንድ ነገር በአንድ ቋንቋ እየተነጋገርን እንዳንግባባ ማስተዋሉን ይነሣናል። እስቲ ራሳችንን እንጠይቅ፤ ከመቅደስ እስከ ዓውደ ምሕረቱ ያለው አገልግሎት በእምነትና በፍቅር ይፈጸማል? በትዳራችን፣ በማኅበራዊ ኑሮአችን፣ በሥራ ገበታችን፣ በጓደኝነታችን ታማኝነትና እውነት አሉ? መታመንን ሰብከን እምነት አጉዳይነትን ገንዘብ ካደረግን፣ ፍቅርን አስተምረን ጥላቻን በልቡናችን ካነገሥን፣ ከእግዚአብሔር፣ ከሕዝብና ከመንግሥት አደራ ተቀብለን አደራ ካጎደልን፣ ዘረኝነትን በአደባባይ ኮንነን በመካከለችን ዘረኝነትን መሸሸጊያ ካደረግን……እግዚአብሔር እንመለስ ዘንድ በትንሹ ይቆነጥጠናል።
ለእኔ አሁን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየሆነ ያለው እገሌ ብለን ጣታችንን የምንቀስርባቸው ሰዎች ያመጡት ሳይሆን የሁላችን የጎጢአት ውጤት ነው ብየ አምናለሁ። ስለዚህ አሁን ጊዜው የመነቃቀፊያ አይደለም፤ የንስሐ እንጂ።

የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በቅርቡ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ታዋድሮስ ካልዓይን መርጣ መሾሟን አብዛኛው ሕዝባችን ያውቀዋል። ብዙዎቻችንም አሁን በቤተ ክርስቲያናችን እየተከሰተ

www.danielkibret.com

ላለው ጊዜያዊ አለመግባባት ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ እንድንወስድ ባገኘነው አጋጣሚ ሐሳብ ስንሰጥ ይስተዋላል። መልካም ነው። ጥሩ ጥሩውን ከጎረቤት መውሰዱ ተገቢ ነው። ታድያ ምሳሌነታቸውን ስንወስድ በመገናኛ ብዙኀን የተገለጠውን ብቻ መሆን የለበትም። ያ ፍጻሜው ያስደስት የነበረው የፓትርያርክ የምርጫ ሥነ ሥርዓት ለዚያ የበቃው በየት በየት አልፎ ነው? ብለንም መጠየቅ ይገባናል።

ባለፈው ኮፕቶች ባደረጉት የፓትርያርክ ምርጫ ለውድድር የቀረቡት አሥራ ሰባት ሰዎች ነበሩ። ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ የቤተ ክርስቲያኒቱን የምርጫ ሕግ አንጠርጥረው ቢያውቁም ምክንያቱን ለማወቅ በማይቻል ሁኔታ ሕጉ ባይፈቅድላቸውም፡ (ለምሳሌ ሀገረ ስብከት ያላቸው፣ ከዚህን ቀደም ፓትርያርክ ለመገልበጥ የሞከሩ) ሳይቀሩ በራሳቸው አነሣሽነት ተመዝግበው እስከ መጨረሻው ድረስ ሲወዳደሩ ነበር። ከእነዚህ ተወዳዳሪዎች መካከልም አንዳንድ የመንግሥት ባለ ሥልጣናትን በመያዝ ዓቃቤ መንበረ ፓትርያርኩን ማለት ብፁዕ አቡነ ጳኩሚዎስን ጫና ሊያደርጉባቸው ያስፈራሯቸው እንደ ነበሩ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ያሰረዳሉ። ሌላ በኩል ደግሞ የወጣቶች ጉዳይ ጳጳስ የሆኑት ተወዳጁ ብፁዕ አቡነ ሙሴን የመሳሰሉት ደግሞ ከአንዴም ሁለቴ እንዲወዳደሩ ቢጠየቁ “እኔ አሁን ዕድሜየ ሰባዎቹ ውስጥ ገብቷል፤ አሁን እኔን ሾማችሁ ገና ደስታችሁን ሳትወጡ ብሞት ለሌላ ድካምና ወጪ ትዳረጋላችሁ። ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ እኔ አባቴ ብፁዕ ወቅዱስ ሺኖዳ ሣልሳዊ በተቀመጠበት መንበር እቀመጥ ዘንድ ብቁ አይደለሁም” ብለው ራሳቸውን ከተወዳዳሪነት ያገለሉ ጀግኖችም ነበሩ።

በአንድ ወቅት ጫናው የበዛባቸው ብፁዕነታቸውም ነገሩ እንዲካረር ለሚያራግቡ የመገናኛ ብዙኀንና ጫናውን በተለያዩ መንገዶች ለሚፈጥሩ የውስጥና የውጪ አካላት ከዚህ ድርጊታቸው ካልታቀቡ እየተደረገ ያለውን ነገር ለሕዝባቸው አስታውቀው ወደ ገዳማቸው እንደሚመለሱ በይፋ ተናገሩ።

አቡነ ጳኩሜዎስ ከዚሁ መግለጫቸው ጎንም በሦስት የተለያዩ ጊዜያት ለሦስት ሦስት ቀናት የሚቆይ የጾምና የጸሎት ጊዜ አውጀው ነበር። እዚህ ላይ ትልቁ ነገር የምሕላ ጊዜ ማወጃቸው ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም የሚገኙ የኮፕቲክ ኦርቶዶክስ አባለት ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጀምሮ እስከ ተራው ምእመን ድረስ እንዲሳተፍበት ያደረጉበት ጥበብ ነው። በእነዚያ የጾምና የጸሎት ዕለታት የጳጳሳቱ፣ የካህናቱና የምእመናኑ ውሎ በቤተ ክርስቲያን ነበር። ይኸ ማለት መላው የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት የሱባኤው ተሳታፊዎች ነበሩ ማለት ነው። ይኸ ማለት ዕለቱን በሰዓታት ከፈለው ሰዓታት ይቆሙበት፣ ጸሎተ ምሕላ ያደርሱበት፣ ቅዳሴ ይቀድሱበት፣ ትምህርት

www.danielkibret.com

ያስተምሩበት፣ ሕዝቡን ያወያዩበት ነበር ማለት ነው። በተለይ በካይሮ በሚገኙ ታላላቅ አድባራትና በሀገሪቱ በሚገኙ ገዳማት ጾሙ ጸሎቱ ይመራ የነበረው በሊቃነ ጳጳሳቱ ነበር። ከሥራቸው ጠባይ የተነሣ በመደበኛው የጸሎት ጊዜ መገኘት ያልቻሉ ሰዎች ወይ የዓመት ፈቃድ ወስደዋል፤ ወይ ደግሞ መላ ሌሊቱን ይደረጉ በነበሩት ጸሎቶች ላይ ተሳትፈዋል።

የሱባኤው በሦስት ጊዜያት መካፋፈል ሁሉም በጉጉት እንዲጠባበቀው ታላቅ አስተዋጽዖ አድርጓል።

እንግዲህ ያ እንደዚያ አምሮና አስለቅሶን የተፈጸመው የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ፩፻፫ኛ ፓትርያርክ ምርጫ እነዚህን ሁሉ ጫናዎች ይኸን በመሰለ ጾምና ጸሎት እንባና ዋይታ መፈጸሙን ልብ በሉልኝ። የእኛስ? እግዚአብሔር ይመስገን ከ20 ዓመታት ቆይታ በኋላ ቅዱስ ሲኖዶሱ የምሕላ ዐወጅ ዐውጆ ነበር። እስቲ ከላይ በገለጥኩት አፈጻጸም መዝኑት። አበውን እንደንነቅፍ አይደለም፤ ለወደፊቱ ግን አንድ ምሕላ ሲታወጅ አስፈጻሚው፣ አፈጻጸሙ፣ ሁሉን አሳታፊነቱ (ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳቱን ሳይቀር) የጊዜው ርዝማኔ.... ከግምት ሊገባ ይገባዋል። ሠራተኛውም ከአባቶቹ ጋር በቤተ ክርስቲያን አድሮ በጸሎቱ እንዲሳተፍ ሁኔታዎች ቢመቻቹለት የእኔነቱን ያጎለብተዋል ብየ አምናለሁ።

ወደ ግብፅ ቤተ ክርስቲያን እንመለስ። ጥቂት ጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳት ሕጉ በማይፈቅድ አካሄድ ለምርጫ መመዝገባቸውን ሕዝቡ የውቅ ነበር። ዓቃቤ መንበረ ፓትርያርኩ ላይ ያደረሱትን ጫና ያውቅ ነበር። ግን ላግልላችሁ አላለም። ሁሉን ወደሚያውቅ ሁሉን ማድረግ ወደሚቻለው ፈጣሪው ግን አነባ፤ ዛሬ ከፉ ብሎ የትናንት መልካም ሥራቸውን አሸቀንጥሮ ገደል ውስጥ አልወረወረም። ዛሬም እንደ ቀድሞው ይወዳቸዋል።

እኛስ? ሰሞኑን የተወሰኑ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት የምርጫውን መዘውር ራሳቸው በፈለጉት መንገድ እየዘወሩት ነው ተብሎ ከመስጋት ያለፈ የትችት ቃላት በአንዳንድ የጡመራ መድረኮች ላይ ስማቸውን ጭምር በመጥቀስ ተሰንዝሮ አየሁ። አሁንም የሌላውን መብት እንዳልጋፋ ፀሐፍያኑ ለምን እንደዚህ አሉ? ብየ አልወቅስም። በርግጥ ፀሐፍያኑ ያንን ነገር ሲጽፉ ለሚቆረቆሩላት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከማሰብ አንጻር ሊሆን ይችላል። ግን አንድ ነገርም እናስተውል። እነዚህ አበው ትናንት ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አንዳች መልካም ሥራ አልሠሩምን? እኒያ ትናንት

www.danielkibret.com

መልካም ሥራ የሠሩ አበው እንደ ሰውነታቸው ደክመው ቢስቱ (መሳሳታቸውን እግዚአብሔር ብቻ ቢያውቀውም) የእኛ መልስ መኰነን ነው ወይ? እነዚህ አበው ከባድ በሆነ ፍቅረ ሢመት ተያዙ እንበልና ልንጸልይላቸው ወይስ ልንጸልይባቸው ነው የሚገባው?

ለቤተ ክርስቲያን፣ ለሃይማኖት፣ ለወገኖች የሚኖረንን ቅናት ገንቢና መንፈሳዊ በሆነ መንገድ ብቻ መግለጥ ያለብን ይመስለኛል። ስሕተት ተፈጽሟል ብለን ስሕተትን በስሕተት ለማረም መነሳሣት አግባብነት የለውም። ያ ከሆነ መጽሐፍ "ኵሉ ዐረየ ውኅቡረ ዐለወ" እንዳለው ይሆንብናል።

ስለዚህ ምን እናድርግ?

1. አባቶቻችን አጠር አጠር ባሉ ጊዜያት የተከፋፈሉ የምሕላ ጊዜያት እንዲያውጁልን እንጠይቅ፤ ምሕላው ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጀምሮ ሁሉን አሳታፊ እንዲሆን ማድረግ
2. ሁላችንም ምሕላውን በንስሐና በፍቅር እንጀምር
   -ምናልባት ሁላችንም ሲባል እንደ ድፍረት ባይቆጠርብኝ። ምክንያቱም አበው "ከገቢር ቢነፁ ከኀልዮ አይነፁ" ይላሉና ነው። እርስ በርሳችን እኔ የኬፋ እኔ የአጵሎስ ብለን ብንጀምረው ፍቅር ስለሚጎድለን ልመናችን ቅድመ መንበሩ አያርግልንምና ነው።
2. አባቶቻችንን ከምንወቅሳቸው በፍቅር ቀርበን መሆን አለበት የምንለውን ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ብናስረዳቸው። ምናልባት እኛ አይተን እነርሱ ያላዩት፣ እነርሱ አይተው እኛ ያላየነው ነገር ሊኖር ይችላልና።
3. ያቅማችንን ፍፁም መንፈሳዊ በሆነና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን በተከተለ አካሄድ ከተወጣን የተቀረውን በሙሉ እምነትና ተስፋ ለእግዚአብሔር እንስጠው
4. ብፁዓን አባቶችም ለመጨረሻው ውሳኔ ሳትቸኩሉ ይኖራሉ ተብለው የሚታሰቡ የመፍትሔ አሳቦች እንዳሉ ከልጆቻችሁ ጋር በመነጋገር አሉ በተባሉ የመፍትሄ አሳቦች ላይ ለመነጋገር ዕድል ስጡ።

   የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ምእመናን ከውስጥ ከውጪ ያሉባቸውን ጫናዎች ተቋቁመው የቀደሙት አበው የሠሩላቸውን ቀኖና አክብረው ለዓለም ጎብረተስብ ቤተ ክርስቲያኒቷ በትክክል በክርስቶስ ዓለትነት መመሥረቷን፣ እነርሱም በትክክል የቅዱሳን አባቶቻቸው ልጆች መሆናቸውን አሳይተዋል። ኢትዮጵያ ሀገራችን የሥልጣኔና የአምልኮ ጀማሪ መሆኗን፣ ሕዝቦቿም ሕግንና ሥርዓትን ጠንቅቀው የሚያውቁና የሚፈጽሙ መሆናቸውን ታላላቅ የዓለም ታሪክ ፀሐፊዎች ሳይቀሩ መስክረዋል።

www.danielkibret.com

እንግዲህ በእግዚአብሔርና በዓለም ሕዝብ ፊት ማንነታችንን የምናሳይበት ጊዜው አሁን ነው። ታሪክ ከመቃብር በላይ ይኖራል። ማንኛውም ዓይነት ሥራችንም በእግዚአብሔር ዘንድ ይቆየናል። ስለዚህ መለያየትን መነቃቀፍን አስወግደን በፍቅርና በእምነት ሰንሰለት ታስረን ለወገኔ ይጠቅማል ሳንል ወይም በጊዜያዊ ነገር ሳንደለል ቤተ ክርስቲያኒቱን ለመጪው ትውልድ ከነ ሙሉ ክብሯ ለማስተላለፍና የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋት የሚያስችለንን የምእመንና (የአማኝ) የባለ አእምሮ ሥራ እንሥራ።

ለዚህም የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት፣ የቅዱሳን ተራዳኢነት አይለየን። አሜን።

ቀሲስ ስንታየሁ አባተ
በግብፅ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ወኪል

www.danielkibret.com